የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፵፫
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፱ ቀን ፪ሺ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No. 43
ADDIS ABABA 6th June 2008

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፶፪/፪ሺ
የኢትዮጵያ የሖርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ….ገጽ ፬ሺ፩፻፲፰

CONTENTS

Regulation No.152/2008
The Ethiopian Horticulture Development Agency Establishment Council of Ministers Regulation ...Page 4118

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፶፪/፪ሺ

## የኢትዮጵያ የሖርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል ።

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ሖርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፶፪/፪ሺ.ህ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ፤

፩. ‹‹ ሖርቲካልቸር›› ማለት አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ አበባና ለህክምናና ለምግብ ማጣፈጫነት የሚውሉ ተክሎችን ይጨምራል፣

፪. ‹‹የሖርቲካልቸር ማህበር›› ማለት የኢትዮጵያ የአትክልት፣ የፍራፍሬና የአበባ አምራችና ላኪዎች ማህበር ማለት ነው፤

፫. ‹‹ግብዓት›› ማለት ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉ ንጥረ ነገሮችና ቁሳቁሶች ያጠቃልላል።

## *COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 152/2008*

## *COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN HORTICULTURE DEVELOPMENT AGENCY*

This Regulation is issued by the Council of Ministers in accordance with Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005.

1. *Short Title*

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Horticulture Development Agency Establishment Council of Ministers Regulation No. 152/2008".

2. *Definitions*

In this Regulation unless the context requires:

1) "Horticulture" includes vegetables, fruits, floriculture and herbs;

2) "Horticulture Association" means the Horticulture Growers and Exporters Association;

3) "Input" means chemicals and materials that help production growth and productivity;

ያንዱ ዋጋ 3.40
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፬. ‹‹ባለድርሻዎች›› ማለት በሆርቲካልቸር ልማት በቀጥታና በተዘዋዋሪ በልማቱ ተሳታፊ የሆኑ የመንግሥትና የግል ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ማህበራትና ሌሎች ሰዎች ናቸው፤

፭. ‹‹የንግድ መሠረተ ልማት›› ማለት የሖርቲካል ቸር ንግዱን ለማሳለጥ የሚያስፈልጉ የመሠ ረተ ልማት ግንባታዎች ናቸው፤

፮. ‹‹የምግብ ደህንነት መስፈርቶች›› ማለት የአት ክልትና ፍራፍሬ ምርት ለሰዎች ጤና ተስማሚ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የወጡ የአገር ውስጥና የውጭ መስፈርቶችን ያጠቃ ልላል፡

፯. ‹‹ዩሮ-ጋፕ›› ማለት የአውሮፓ ሕብረት የግብርና ሰብሎች አመራረትና እንክብካቤ የጥራት መስፈርት ነው፤

፰. ‹‹ክልል›› ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፵፯ (፩) ላይ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፱. ‹‹ሚኒስቴር›› ወይም ‹‹ሚኒስትር›› ማለት እንደቅደም ተከተሉ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፲. ‹‹ሰው›› ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፫. መቋቋም

፩. የኢትዮጵያ የሖርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ ‹‹ኤጀንሲ›› እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራሉ መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪ ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

፬. የኤጀንሲው ዓላማ

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

፩. የሖርቲካልቸር ምርትና ምርታማነት በተፋጠ ነና በቀጣይነት እንዲያድግ የማብቃት፣

፪. ዓለም አቀፍ የምግብ ደህንነት መስፈርቶችን የሚያሟሉ የሖርቲካልቸር ምርቶች ለውጭ ገበያ በዓይነትና በብዛት የሚቀርቡበትን ሁኔታ የማመቻቸት፤ እና

፫. ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶችን ያስተባብራል፡፡

4) "Stakeholders" means government and private organizations, that participate directly or indirectly in horticulture development, non-governmental organizations, associations and other persons ;

5) "Trade Infrastructure" means infrastructure facilities required for conducting efficient horticulture trade;

6) "Food Safety Standards" include domestic and foreign standards enacted to ensure the safety of vegetables and fruits for human consumption;

7) "Euro-gap" means European's quality standard for agriculture produce;

8) "Region" means any region referred to in Article 47 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes Addis Ababa and Diredawa City Administrations;

9) "Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minister of Agriculture and Rural Development respectively;

10) "Person" means any physical or juridical person.

3. *Establishement*

1) The Ethiopian Horticulture Development Agenc (hereinafter the "Agenecy") is hereby establishe as an autonomous Federal Government Agenc having its own legal personality.

2) The Agency shall be accountable to the Ministry.

4. *Objectives*

The Agency shall have the following objectives:

1) to ensure the fast and sustainable growth of horticulture production and productivity;

2) to facilitate the export of diversified horticultu products which meet internal food safe standards; and

3) to coordinate the development of supporti services.

፭. <u>የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባራት</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. የሖርቲካልቸርን ዘርፍ ፈጣን ዕድገትና ቀጣ ይነት ለማረጋገጥ የሚያግዝ ስትራቴጂ አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፤

፪. በሖርቲካልቸር ልማት ለሚሰማሩት ባለሀብቶች ለአዋጭነት ጥናት መረጃ ይሰጣል፣ ከክልል አካላት ጋር በመተባበር መሬትና የግንባታ ፈቃድ እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፤ አፈጻ ጸሙን ይከታተላል፤

፫. የመሠረተ ልማት በወቅቱ እንዲያገኙ ለግንባታው ከውጭ አገር የሚገዙ ግብዓቶች ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ከአገር ውስጥ የሚገዙትን የግንባታ ዕቃዎች በወቅቱ እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፤ የግንባታውን አፈጻጸም ይከታተላል፤

፬. የግብዓት አቅርቦትና አገልግሎት የሚሻሻልበትን ሁኔታ በማጥናት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

፭. በሖርቲካልቸር ልማት ከአርሶአደሩ ጋር ተዋውለው ለመሰማራት የሚፈልጉትን ባለ ሀብቶች ከክልሎችና ከአርሶ አደር ማህበራት ጋር በመተባበር በአርሶ አደር ምልመላና አደረጃጀት ያግዛል፣ ስለዩሮ-ጋፕ ሥልጠና ይሰጣል፣ የአሰራር ማኑዋል ያዘጋጃል፣ አፈጻ ጸሙን ይከታተላል፤

፮. ከክልል የሠራተኛ ጉዳይ ጽሕፈት ቤቶች ጋር በመተባበር የሰው ኃይል አቅርቦት እንዲመቻች ያደርጋል፤

፯. የሖርቲካልቸር ኤክስፖርት ምርቶች በዋጋና በጥራት ተወዳዳሪነታቸውን ለማረጋገጥ ከሌ ሎች ሀገሮች ተሞክሮ በመነሳት ስለተሻለ አመራረት፣ ምርት እንክብካቤ፣ ጥራትና የም ግብ ደህንነት ከሖርቲካልቸር ማህበር ጋር በመተባበር ሥልጠናና የምክር አገልግሎት ይሰጣል የመስፈርቶችና የኤክስቴንሽን ፓኬጆ ችና ማኑዋሎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤

፰. ጥራቱን የጠበቀ የንግድ የመሠረተ ልማት ግንባታ፣ ድጋፍ ሰጪ ተቋሞችና አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ከሚመለከታቸው ጋር የተባበራል፤

፱. ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሎጂስቲክስ ፍላጎት ጥናት በማካሄድ የውሳኔ ሀሳብ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ነቱን ይከታተላል፤

5. *Powers and Duties of the Agency*

The Agency shall have the powers and duties to:

1) prepare and submit to the Ministry a strategy which ensures fast and sustainable growth of horticulture and, upon approval, follow up the implementation of the same;

2) provide necessary information to investors undertaking horticulture development feasibility studies and, in cooperation with regional administrations, facilitate access to land and acquisition of construction permits and follow up its implementation;

3) assist investors in the clearance of imported construction materials and the timely acquisition of local construction materials so that they will be able to have, in due time , the necessary infrastructure facilities, and follow up the construction of the same;

4) undertake, and submit to the Ministry, studies to improve the supply of inputs and related services, and follow up its implementation upon approval;

5) in cooperation with regional administrations and farmers cooperatives, assist investors wishing to engage in horticulture development, through out growers schemes, in selecting and organizing farmers for such scheme; train farmers in Euro-gap, prepare operational manual and follow up its implementation;

6) facilitate the supply of man power in cooperation with regional labor offices;

7) in cooperation with horticulture association, provide to horticultural farms training and advisory services on best agricultural practice, quality and food safety standards and prepare standards and extension packages and manuals based on best practices of other countries in order to ensure price and quality competitive horticulture exports;

8) cooperate with concerned bodies for the development of quality trade infrastructure and the expansion of support services and institutions;

9) undertake studies on vegetables and fruits logistic demand and submit is recommendations to the Ministry, and follow up its implementation upon approval;

፲. የሖርቲካልቸር ዘር አልሚዎች ወደ ኢትዮጵያ በስፋት የሚገቡበትን ሁኔታ በማጥናት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

፲፩. የሖርቲካልቸር ገበያ ጥናት ያካሂዳል፣ የገበያ መረጃዎችን የሰበስባል፣ ያሰራጫል፣ የሖርቲካልቸር አምራችና ላኪዎች በዓለም አቀፍ ንግድ ትርዒቶች ላይ እንዲሳተፉ ሁኔታዎች ያመቻቻል፤

፲፪. የሖርቲካልቸር ማህበርና ሌሎች ባለድርሻዎች የሚሳተፉበት ቋሚ መድረክ በማቋቋም በጋራ ለልማቱ የሚያግዙ እርምጃዎችን ይወስዳል፤ የሆርቲካልቸር ልማት ፕሮግራሞችን ያስተባብራል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

፲፫. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፲፬. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ሕጋዊ ተግባራትን ያከናውናል።

፮. የኤጀንሲ አቋም

ኤጀንሲው፤

፩. በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተር፣ እና

፪. አስፈላጊው ሠራተኞች

ይኖሩታል፤

፯. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩. ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፤

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ ዓላማ ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት የኤጀንሲውን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኤጀንሲውን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

10) undertake, and submit to the Ministry, studies on ways and means of attracting horticulture breeders to come to Ethiopia, and follow up its implementation upon approval;

11) undertake horticulture market studies, and collect and disseminate market information; facilitate the participation of horticulture producers and exporters in international trade fairs;

12) establish a forum of consultation with horticulture association and other stakeholders and take measures that provide common support to the horticulture development; coordinate and follow up the implementation of the programs.

13) own properties, enter into contacts, sue and be sued in its own name;

14) undertake other lawful activities that are conducive to the fulfillment of its objectives.

6. *Organization of the Agency*

The Agency shall have:

1) a Director General to be appointed by the Government upon the recommendation of the Minister; and

2) the necessary staff.

7. *Powers and Duties of the Director General*

1) The Director General shall be the chief executive officer of the Agency and shall, subject to the general directives of the Ministry, direct administer and control the activities of the agency.

2) Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the Director General shall:

(a) exercise the powers and duties of the Agency stated under Article 5 of this Regulation;

(b) employ and administer employees of the Agency in accordance with directives to be approved by the Government following the basic principles of the federal civil service laws;

(c) prepare and submit to the Ministry the work program and budget of the Agency, and implement the same upon approval;

መ) ለኤጀንሲው በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ረ) የኤጀንሲውን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

ሰ) በሚኒስቴሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

፫. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

፰. በጀት

የኤጀንሲው በጀት በፌዴራል መንግሥት ይመደባል።

፱. ስለሂሳብ መዛግብት

፩. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።

፪. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

፲. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፳፱ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም.

**መለስ ዜናዊ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

(d) effect expenditure in accordance with the approved budget and work program of the Agency;

(e) represent the Agency in all its dealings with third parties;

(f) prepare and submit to the Ministry the activity and financial reports of the Agency;

(g) perform other functions as may be assigned to him by the Ministry.

3. The Director General may delegate part of his powers and duties to other officers and staff of the Agency to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Agency.

8. *Budget*

The Agency's budget shall be allocated by the Federal Government.

9. *Books of Accounts*

1) The agency shall keep complete and accurate books of accounts.

2) The books of accounts of the Agency shall be audited annually by the Auditor General or by auditors assigned by the Auditor General.

10. *Effective Date*

This Regulation shall come into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa this 6th day of June, 2008.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA